ጠያቂ፡- ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሺ/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?

ተጠያቂ፡- ስሜ ጽዮን እባላለው ሦስት ወር ሳይሆን በትክክል ወሩን ልሳሳት እችላለሁ ወቅት የማረሳቸው ከዛን ትመድበዋለክ መስከረም የምሽቶች እና የቀን ፋሬሽን ኢንተርፋሩ እኩል ይሆናል አየሩ እራሱ ቺት የሆነ ቢግኒንግ ፍሬሽ የሆነ ከነ ጠረኑ ከነ ድባቡ እንደ አዲስ ነገር መጀመሪያ ከዛ ደግሞ ክረምት ሲገባ ሐምሌ ዝናብ አፈሩን ሲነካ የሚፈጥረው ሽታ ባይሎጂካል ቅሽምና ነው ግን የሆነ ጭንቅላትክ ውስጥ ……ከዛ ጳጎሜ ምን ወር ላይ ነው ግን ፀበል እሩፋኤል እሱ ቀን ዮኸሊ መርመርበል ነው ታየዋለክ ከተማ ውስጥ 6 ቀን ስለሆነ ዩርድ ስለሆነ ኦኬ የሚምታታምክ ሰዓት ላይክ ደስ ይላል፡፡

ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ

ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሽው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?

ተጠያቂ፡- እሺ ዳንኤል አበራ እባላለሁ እና ለእኔ ሚሞሬብል የሆነው ጥር ወር ነው ጥር ወር ሚሞሬብል የሆነው አንደኛ የተወድኩበት ወር ነው ጥር 19 የተወለድኩት በልደት ቀን የምታሳልፋቸው ነገሮች ….እነዛ ጥር ወርን ስሜት እንዲሰጡ እንደገና ጥምቀት የሚባል ባህል አለ በዚሁ ላይ ያሉ ሚሞሪዎች ጥር ወር ለእኔ ሸጋ ወር ነው ከነዚህ ከነዚህ ነገሮች አንጻር ለእኔ ጥር ወር

ጠያቂ፡- ሌላ ተጨማሪ?

ተጠያቂ፡- ሌላ ደግሞ መስከረም ደግሞ ትምህርት የሚጀመርበት በአዲስ ስሜት የምትመጣበት ከክረምት አልፎ ልክ መስከረም ሲመጣ ያ ስሜት አለው አዲስ የሆነ ስሜት ካለፈው አመት ወደዚህኛው አመት ስትመጣ እና መስረከም እና ጥር ለእኔ ሚሞሪብል የሆኑ እና ቆንጆ ወራቶች ናቸው፡፡

**ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ**

**ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሸው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?**

ተጠያቂ፡- እኔ ስሜ እፁብቀለመ ወርቅ ይባላል እና ከ13 ወሮች ለእኔ ስሜት የሚሰጠው ደስ የሚለኝ ከበጋ በኃላ ክረምት ነው ክላስ ይዘጋል ክላስ በሚዘጋበት ጊዜ ደግሞ ከቤተሰቦች ጋር ሞር ለእኔ ደስ ይለኛል ከሰኔ በኃላ ሰኔ፣ ሐምሌ፣ ነሐሴ እነዛ ደስ ይሉኛል፡፡

**ጠያቂ፡- እስፔስፐካሊ**

ተጠያቂ፡- እስፔስፐካሊ ሐምሌ ደስ ይለኛል ምክንያቱም የቤተሰቦቼ የእህቴ ልደት እዛ አካባቢ ስለሆነ የጎደኛዬም እንደዛው እና ሐምሌ ደስ ይለኛል፤ አመሰግናለሁ፡፡

**ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ**

**ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሽው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?**

ተጠያቂ፡- ስሜ ተስፋሚካኤል ታፈሰ ይባላል ለእኔ እንግዲ ሚሞሬብል ብዬ የማስበው መስከረም ነው ያው ከምን አንፃር ሲባልም ያው መስረከም የአዝመራ ወቅት እህል የሚበቅልበት እንደ አዲስ አመቱ እንደ አዲስ የምንጀምርበት ወቅት እንደመሆኑ መጠን መስከረም በጣም ስሜት አለው ለእኔ እንደገና ከእሱ በተጨማሪ እኛ ሀገር በደንብ አያከበርም እንጂ በውጭ ሀገር ደሞ ከፍተኛ አከባበር የሚደረግበት ያው መስረከም ከዚህ አንጻር ለእኔ ስሜት አለው፤

**ጠያቂ፡- ሌላ ወር አለው?**

ተጠያቂ፡- ለጊዜው ይኸ ነው ያለኝ፤

**ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሽው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?**

ተጠያቂ፡- ስሜ አሸናፊ ማሩ ነው ከእኔ ጋር ሪሌት የሚያደርገው ወይም ደግሞ እኔን ይገልጸኛል ብዬ የማስበው መስከረም ወር ነው ለምንድነው ነገሮች የሚያልቁበት እና እንደ አዲስ ነገር ለመጀመር እድል የምናገኝበት ስለሆነ ነው የሆነ ነገር እስታክ አድርጎ የሚጀመርበት ስለሆነ ነው ሌላው ደግሞ በጣም የሚያስለቸኝ ወይም ባይኖር የምለው መጋቢት ወር ነው ምንድነው ሚድ ላይ ስለሆነ ክላሱንም ኖርማል ላይፍ ላይም ቢሆን በጣም ቻሌንጅ የሚኖርበት ነው ከአየሩም እንዲሁም ደሞ ጾም ስለሆነ በጣም ባይኖር ደስ ይለኛል፡፡

ጠያቂ፡- ሌላ አለህ?

ተጠያቂ፡- ሌላ የለኝም

ጠያቂ፡- እሺ አመሰግናለሁ፡፡

ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሽው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?

ተጠያቂ፡- ስሜ አቤል ቡቼሉ ይባላል ሞር ለእኔ ስሜት ያለው ወር በተለይ ህፃን እያለው ክረምት በጣምው በጣም ነው ደስ የሚለኝ ወሮች ናቸው

ጠያቂ፡- የትኛው ወር?

ተጠያቂ፡- ከሰኔ በኃላ ያሉት በተለይ ነሐሴ በጣም ነው ደስ የሚለኝ ጊዜ ነው ከክላስ እናርፋለን መጫወትም አየሩም ክረምቱም ጭቃው ሁሉ ነገር በጣም ደስ የሚለኝ ጊዜ ነው አሁን አሁን ላይ ደሞ ጥርን በጣም እወደዋለሁ የእናቴ የልደት ወር ስለሆነ በጣም ነው የሚጠብቀው ወር ነው ለእኔም ለብዙም ነገር እሷም ብዙ ነገር ስላደረገችልኝ የምጠብቀው እና ደስ የሚለኝ ወር ጥር ነው ከዛም ያው እነ ነሐሴ በጣም ነው የምወዳቸው የልጅነት ብዙ ሚሞሪ ስላላቸው ነሐሴ እና ጥር

ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ

ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሽው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?

ተጠያቂ፡- ስሜ አክሊሉ ግርማ ይባላል ከ13 ወራት ውስጥ ለእኔ ትልቅ ደስታ እና ትርጉም ያለው መስከረም ወርን በጣም እወደዋለሁ አንደኛ የአዲስ ዓመት መግቢያ ነው ሁለተኛ ያው ልደቴ በዛ ውስጥ ነው የተወለድኩበት ነው ይህንን አለም የተቀላቀልኩበት ነው ሌላው ደሞ በዓላቶች አሉ መስቀልን በጣም ነው የምወደው በዓል ነው በዛ ውስጥ ስለሆነ መስከረም በጣም ደስ ይለኛል በተቃራኒ መጥፎ ሚሞሪ ያለው መጋቢት ወር አልወደውም መጋቢት ወር ለእኔ በጣም ከባድ ነው ሁለት ሰዎችን አጥቼበታለው እንደ እኔ አያቴ እና አባቴን በአንድ ወር ውስጥ ነው ያጣውት በአንድ አመት ልዩነት ውስጥ መጋቢት ወር ሲመጣ መጥፎ ስሜቶች መጥፎ ትዝታዎች ስላሉት መጋቢት ወር ይከብደኛል ለእኔ

ጠያቂ፡- ሌላ ወር አለህ ሌላ ሞሚሪ

ተጠያቂ፡- ሌላ ወር እንዲው ዝም ብሎ ጳጉሜ ደስ ይለኛል ከጓደኞቼ ጋር የማሳልፈው ወር ጳጉሜ ጥምቀት የሚባለው በጣም ደስ ይለኛል ትስበኛለች አጭር ናት ሌሎች ጊዜ ናት አመሰግናለሁ፡፡

ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡

ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሽው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?

ተጠያቂ፡- እሺ በጣም በጣም ደስ ከሚለኝ ኦ ስሜ ዳን ግርማ ይባላል እግዚአብሔር ይስጥልኝ በጣም ደስ የሚለኝ ወር መጀመሪያ የተወለድኩበት ሰኔ  በጣም ደስ ይለኛል ከዛ ቀጥሎ ያለው ደሞ ብርሃማ የሆኑትን 6 ወራት ከመስከረም እስከ የካቲት ያለው ከዛ በኃላ እንኳን በጣም መስረከም ጥቅምት ህዳር ታህሳስ ጥር እያለ የሚሄደው እስከ ፈርስት ሴሚስቴር እንደ ምትለው በክላስ ሲዩም በጣም ደስ የሚል ነው ከዛ በኃላ እንኳን በሁለቱም ሚክስድ ስለሆነ ይሄ ነው ለማለት አልችልም ላይክ አይያዝም ባህሪው ይዘንባልም ፀሐይም ያቃጥላልም እንደት አይልም ደስ አይልም መጥበሻ ላይ ነው ያንን ስሜት የሚሰው ይኸው ግን በደንብ የብርሃን እንት ነው ያለው ይኸ የክረምት ኩዚ ካራክተሩን አጥፉቶት ሌላ ብርሃን ሌላ ሀሳብ ሌላ መንገድ  በአዲስ ሰው ልክ በዓል ጋር የሚነሳበት መንገድ አይደል ልክ እንደዚህ አይነት ስሜት ይሰማል እና እሱ ነገር ደስ ይለኛል፡፡

**ጠያቂ፡- ሌላ ወር የምትነግረኝ አለህ?**

ተጠያቂ፡- መስከረም በዓል ጋር አያይዥው ወይ የዓመት መጀመሪያ ሳይሆን በቃ ዝም ብለህ የመጀመሪያ ልጄ  አይን የሚገልጥልክ እንደ እንደማለት ነው ስለዚህ ሰው የሚገልጥበት ሰኞ እንደማለት መስረከም እንደ እዛ ነው የሚሰማኝ ከዛ ደሞ ማክሰኞች እሮብ እያልክ እንደሚትቆጥረው ጥቅምት ህዳር እያለ ለቀን በአንዱ አንዱ የወለደውን የሚሄደውን ፕሮግረስህን የምታዳምጥበት ይሆናል ማለት ነው ሰኞ ማነው በእረፍት ቀን ያላሰብከውን በስራ ቀን ቆመህ ስለ ስራ አታስብም የምትሰራበት ሰዓት ይሆናል ማለት ነው ከዛ በኃላ ማረፍ በሚገባ ሰዓት ታርፉህ ውችሚዝ የክረምት ሰዓት ይሆናል ማለት በክረምት ሰዓት ደሞ አታርስም እንደ እዛ አይነት ስሜት

ጠያቂ፡- ስለዚህ መስረከም ልበለው

ተጠያቂ፡- በለው መስረከም ብለው ሰኞ እንደማለት ኖሞር ብላክ መንደይ

ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሸው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?

ተጠያቂ፡- ስሜ እሺ ኑሃሚን እባላለው ሚሞሬብል በሚለው እንያዘው እና ሐምሌ ሰኔ እና ጥር ሶ ሐምሌ ያው የተወለድኩበት ወር ስለሆነ ሰኔ ደሞ አብዛኛው …….እስከ ጓደኞቼ ሰኔ የተወለድባቸው አብዛኞቹ ጥር ብዙ ነገር አፐን የሆነበት ነው የሚባለው ፐርሰናል እንደዛ አይነት ወር ነው፡፡

ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡

ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሸው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?

ተጠያቂ፡- ስሜ ፔፐሲ ይባላል እንዳልከው ሚሞሪብል ከሆኑት መካከል …………ወይ ልደት ወይ በዓል የሆነ ነው ሙሉ ወሩን የሚገልጸው አንድ ቀን ናት ለምሳሌ የእኔ ልደት ህዳር ወር ውስጥ ነው ከጓደኞቼ ጋር እንዳልከው ደስ የሚል ጊዜ የማሳልፍበት እና አይ ዶኖ ኒሞሪብል የሆበት ምክንያቱም ያ ቀን ኒሞብል ይሆናል ከእሱ

ውጪ ደሞ የጓደኞቼ ልደት ኖብል ማለት በቃ ሙሉ አመቱን ........እሱም እንደ አሁን የእሷ ግንቦት መጨረሻ አካባቢ ነው ከዛ በኃላ የሌላ ጓደኞችን ደሞ መጋቢት ውስጥ ነው መጋቢት 7 እና እሱን እነዚህ ሦስት ወራት መጋቢት፣ ህዳር እና ግንቦት ሞሚሪብል ነው ለእኔ

**ጠያቂ፡- ጥሩ ጊዜ የምታሳልፊበት እና የተለየ ጊዜ ነው እንበለው?**

ተጠያቂ፡- ከዛ ውጪ ደሞ መስረከም

**ጠያቂ፡- እስኪ ስለመስረከም ትንሽ ነገር በይን?**

ተጠያቂ፡- መስረከም ደሞ እንትል አዲስ አመት የሚባል ስለሆነ አራቱ ወር መስረከም ህዳር፣ መጋቢት፣ ግንቦት

**ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡**

**ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሽው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?**

ተጠያቂ፡- ስሜ ሳሮን ይባላል ከ13 ወራቶች ውስጥ ልደት ነው ደስ የሚለው አንዱ ቀን ዲፋይን የሚታደርገው ከዛ ውስጥ ህዳር ላይ ብዙ ጓደኞቼ ህዳር ላይ ጥር ላይ የራሴን ግንቦት ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ድረስ ነው የማከብረው ከዛ ውጪ የካቲት እና መጋቢት ደስ ይለኛል በአብዛኛዎቹ ብዙ ወሮቹ ደስ ይለኛል እውነት ለመናገር ሚሞሪበል ናቸው እያንዳንዱ ወር ላይ የሆነ ነገር ይኖራል፡፡ ከበዓላት ግን ገና ደስ ይለኛል የሆነ ፊሊንግ አለው አይ ዶኖ ሚቢ የውጭ ሙቪዎችን እያየን ስላደግን ይሆናል ላይክ ስሎ

ኢትዮጵያ ውስጥ የለም አክሺሊ ግን ደግሞ የራሳችን የሆነ ባህል አለን እና ባህላዊ ስሜቱ የሆነ ፊሊንግ አለው ቤተ ክርስቲያን ሄዶ ማደሩ የሚፈጥሩት ነገር ገና ከበዓላት በጣም ደስ ይለኛል፡፡

**ጠያቂ፡- ምን ወር ላይ ነው?**

ተጠያቂ፡- ታህሳስ በጣም ደስ ይለኛል ምንም አፕን ቢያደርግ ገና በጣም ደስ ይለኛል፡፡ ታህሳስ ወሯ ከዛ ውጪ የካቲት መጋቢት ሚያዚያ ግንቦት ህዳር እና ጥር እነዚህ ሁሉ ላይ የጓደኞቼ ልደት ያሉበት ነው ለእኔ ላይክ ለጓደኞቼ ስጦታ ከመስጠት የላቀ አብሬሼሽን ደይ ነው ላይክ እኔ ማድረግ የምፈልጋቸውን ነገር ነው ለእሱ ማድረገው እና አመቱን ሙሉ …………ጥሩ ሰው የምትልበት ቀን ስለሆነ የነሱን ወራቶች ደስ ይሉኛል፡፡

**ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡**

**ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሽው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?**

ተጠያቂ፡- ስሜ ጃጀፌሳ ይባላል በጣም ትዝ የሚለኝ ወር ማለትም ፊሊንግ የሚሰጠኝ ወር ግንቦት ነው 20 በጣም ትዝ ይለኛል ከወራቶቹ ውስጥ ለማለት ትዝ የሚል ነገር አለ አብዛኛውን ጊዜ የመንግስት በዓላት እኛ ሀገር የሚበዛው የአብአደሮች ቀን ትምህርት ቤት ሲሰጋ የካቲት አብዛኛው ወራቶች አሉት እና እንደዚአይነት እንትኖች ነው ፊል የማደርገው ስፔሻል የልደቴን ቀን ሰኔ ወር እና የምልህ አለ አይደል እነኚ ፐርሰናል የምታስባቸው ነገሮች አሉ በራሴ አሁን ለምሳሌ መስከረም መስቀል አለ ከዛ በኃላ ጥቅምት አለ ጥር

ያስታውስሃል ሁሉም ሚሞሪ ነው ገባህ በየወሩ በየወሩ የራሳቸው የራስህ ወሮች ይኖራሉ እንዲቪገሮል ማለት ነው ለራሴ ስፔሻል ወር የምለው ሰኔ ወር የተወለድኩበት የማትረሳው ማለት ነው

**ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡**

**ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሺው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?**

ተጠያቂ፡- ስሜ ምህረት መክብብ ነው እና ከ13 ወሮች ቫሊ የማደርጋቸው መስከረም እና ግንቦት ነው መስረከም የአመቱ ጅማሪ ነው ብዙ ነገር የምናስተካክልበት ነው እና በመስረከም ወር ነው የተወለድኩት ብዙ ሚሞሪዎች ያሉኝ በመስከረም ላይ ነው ግንቦትን ደሞ አድ የማደርገበት ወላጆቼ የተጋቡበት ወር ስለሆነ ነው ወላጆቼም እህቴም ያገባችሁ ግንቦት ነው እኔም ማግባት የምፈልገው ግንቦት ነው ሁለቱን ወር የምመርጠው

**ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡**

**ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሺው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?**

ተጠያቂ፡- ስሜ ሂንዲንያ ይባላል ሁለት ወሮችን ነው ቫሊ የማደርገው መስረከም እና ጳጉሜን መስረከም ያው አዲስ አመት

እንደመጀመሪያው ነው በተጨማሪም ደሞ እንቁጣጣሽን በዓል በጣም ነው የምወደው እና አዲስ ፕላን ብዙ ነገር የምጀመርበት ስለሆነ እወደዋለሁ ጳጉሜን ደሞ የአመቱ መጨረሻ እንደመሆኑ ወደ ሚቀጥለው ዓመት ማስተላለፍ የማልፈልጋቸውን ብዙ ነገሮች ማስተካከል ይቅርታ ማድረግ ብዙ ነገሮችን ማድረግበት ስለሆነ እወደዋለሁ፡፡

**ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡**

**ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሽው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?**

ተጠያቂ፡- ስሜ ሆፕ እባላለው ከኢትዮጵያ ወራቶች ሰኔን እመርጣለሁ፡፡ ክረምት ላይ ነው ሰኔ የክረምት መግቢያ ነው ዝናብ ይመቸኛል ሶው

**ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡**

**ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሽው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?**

**ተጠያቂ፡-** ስሜ ኤልሳቤት ዮናስ ይባላል አቲንግ ከኢትዮጵያ ወራቶች ደስ የሚለኝ መስረከም ነው ቢኮዝ የአመቱ መጀመሪያ ነው ሲቀጥል

የተወለድኩበት ወር ነው ሶው ያው ለሰው ብዙ እቅድ የማወጣበት አመቴ የማቅድበት አዲስ ስታርቲንግ የሚሰማኝ ስለሆነ መስረከምን እወዳለው

**ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡**

**ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሽው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?**

ተጠያቂ፡- ስሜ ዮሀንስ እባላለሁ ከ13 ወሮች ውስጥ ጳጉሜ ደስ ትለኛለች ምክንያቱም ያው አጠር ያለች ከሌሎች ለየት ያለች ስለሆነች በጣም ደስ ትላለች ሌላ ሚሞሬብል የሆነ ነገር የለኝም

**ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡**

**ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሽው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?**

ተጠያቂ፡- ስሜ ዴንዲቲ መኮንን ይባላል ሁለት ወር መምረጥ ብችል ሚያዚያ እና ግንቦት በጣም ነው የምወዳቸው አንደኛ ግንቦት የተወለድኩበት ሚያዚያና ግንቦት ደሞ በብዛት እረመዳን የሚሆንበት ጊዜ ስለሆነ ቤተሰብ የሚሰባሰብበት ጊዜ ነው ሶሻል ኢንተራክሽን የሚበዛበት ጊዜ ነው በጣም የሚመቸኝ ሁለቱ ናቸው

**ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡**

ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሸው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?

ተጠያቂ፡- ስሜ ኦኬ ስሜ ፍቅር ይባላል ጥምቀት ጥር ላይ ደስ ይባላል ግርግሩ ላይክ ቤተ ክርስቲያን ስትሄድ ዝማሬው ደስ ይላል ለእኔ እስፔክስፊክ ደግሞ ነሐሴ ደስ ይለኛል አይ ጉይንግ ቱ ሰልፍሽ ልደቴ ነው ነሐሴ ትምህርት የለም ቤት ትተኛለህ ዝናብ አለ ፊልም ታያለህ ከቤተሰብ ጋር ሌላው ደግሞ ግንቦት በፀሀይ ጌታ ሆይ በጣም ነው የሚያቃጥለው ግንቦት ላይ ትዝ የሚለኝ ጥቅምት ደግሞ አይ እስኩል ላይ ስንማር እንሰለፍ ነበር ጠዋት ጠዋት ሰልፊ ብርዱ በጣም አይለኛ ነው፡፡

ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡

ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሸው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?

ተጠያቂ፡- ስሜ ዮሐንስ እባላለሁ ግንቦት ነው ግንቦት ደግሞ በጣም የምወዳትን ልጅ የተዋወቁበት ቀን ያ ቀን ያ ወር እስፔሻል የመጀመሪያ ዓመት ነው፡፡

ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡

ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሸው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?

ተጠያቂ፡- ስሜ ዳግማዊ እባላለው ሚሞሪብል ወሮች የልደቴ ቀን ነው የልደቴ ቀን የመስቀል ቀን ስለሆነ ሶልቫይቪ በጣም ደስ ይላል እሱ እና ደሞ መስከረም ዘ ፊርስት ቫይ ኮምፕትሽን ላይ በሕይወቴ ትልቁ ነገር ማድረግ የምፈልገው መጀመሪያ ኮምፕትሽን ኮምፕት አድርጌ ያለፍኩበት ወር ነው በተጨማሪ ለመጀመሪያ ጊዜ ያፈቅርኩበት ቀን ነው መስረከም 1 ጀምሮ እስከ መስረከም መጨረሻ ያለው ወር ለእኔ በደንብ ኢንጆይ አድርጌዋለው ሁኔታ በየአመቱ ኢንጆይ ማደርግበት ወር ነው በዛው ልክ በአድ ነገሮች አፕን የሚያደርገበት ምፈልጋቸው ሰዎች ያጣውበት ቀን እና በአድ ሚሞሪ ስላለኝ በጥሩ ነገር ማሳለፍ የምፈልገው

ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡

ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሸው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?

ተጠያቂ፡- ሚሞሪብል እንጃ ከ13 ወሮች ልደቴ አለ ግን ሞር እሱ ሳይሆን ከክላስ አንጻር አንድ ሳምንት ይዘጋልን ነበር የትንሳኤ ሰሞን አለ አይደል እስከ እሁድ እሱ እሱ ነገር ደስ ይለኝ ነበር ሰኔ ደሞ የወላጆች ቀን ነበር እና ከፋዘር ጋር ነበር የምንሄደው ኤሞስቲሊ ከእሱ ጋር መሆኑ እንጆይ አደርገው ነበር ከ1-3 ስጦታ አይደል ከፋዘር ጋር ነው የምንሄደው በጣም ደስ ይለኝ ነበር እና ሰኔ አመሰግናለሁ፡፡

ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡

ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሸው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?

ተጠያቂ፡- ስሜ ቤተል ጌቱ እባላለሁ ለእኔ ከ13 ወሮች ውስጥ ነሐሴ አንደኛ የተወለድኩበት ወር ነው ሁለተኛ ክረምት ላይ ብዙ ሰው እንደዛነው ሊል የሚችለው በጣም ብዙ ሰው ሚሞሪ ሊኖረው የሚችለው ክረምት ላይ ነው ተማሪዎች እረፍት የሚኖራቸው ኳስ የሚጫወቱት ጭቃ ውስጥ ጭቃ እያቦኩ ብዙ ነገር ትዝታ የሚኖራቸው ትዝታን ስትስል ሬኒ ነው የምታደርገው ሶ ብዙ ትዝታ የሚኖረው ክረምት ውስጥ ነው ብዬ ስለማስብ ነሐሴ ትዝታ ውስጥ ይከተኛል ደስ ይለኛል በጣም

ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡

ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሸው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?

ተጠያቂ፡- ኦኬ አመስግናለሁ እዮብ እባላለሁ ከ13 ወራት ውስጥ በጣም ሚሞሬብል የሆነው ታህሳስ ወር በጣም ይመቸኛል እሱንም ያልኩበት ምክንያት የእህቴም የእኔም እና የወንድሜ ልደት ስለሆነ ታህሳስ ወር በጣም የምወደው ወር ሌላው ጳጉሜ ወር ነው ዘመን መሻገሪያ ስለሆነች በጣም አጭር ናት የባህሉ ድባቡ አለ

የምናሳልፍበት በዛች አምስት ቀን ውስጥ የባህል ስሜት ያለበት ታይም አለ በጣም የምወዳቸው ወራቶች እነዚህ ናቸው ሁለቱን ነው በጣም የምወዳቸው

**ጠያቂ፡- ሌላ አለህ?**

**ተጠያቂ**፡- ሌላ የለም ሁለቱ ወሮች ናቸው፡፡

**ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡**

**ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሽው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?**

ተጠያቂ፡- ክብሮም ስዩም እባላለሁ ሁለት ወሮች አንዱ መስረከም ነው ሌላው ደሞ ነሐሴ ክረምት ያለበት ወር መስረከም ያው መስረከም አንድ ስለተወለድኩኝ ነው ልደቴን ያከብርኩት እስከ 9 ዓመቴ ድረስ ነው ያከበርኩት ከዛን እያደኩኝ በሄድኩ ቁጥር ያው አልተከበረም እኔም በስራ ምክንያት ከቤተሰቦቼ ጋር ስላነበርኩኝ ከዛን ፊል የማደርገው መስረከም አንድ አዲስ አመት ሁሉም ኢትዮጵያ የሚያከብረው ይመስለኛል፡፡ ልደቴን ማለቴ ነው አንድ እሱ ነው ኦኬ ዛሬ መስረከም አንድ ነው እየተከበረልኝ ነው እላለሁ ማለት ነው አንዳንድ ጊዜ እየተከበረልኝ ነው ብሉ ጠጡ እላለሁ ቤት ሆኜ ልሆን ይችላል ለብቻዬም ቁጭ ብዬ ሊሆን ይችላል ግን ብሉ ጠጡ እላለሁ ጥሩ ስሜት ያለው ዝናብ ሲመጣ በብርድ ልብስ ተከናምበ ስተኛ ያለው ስሜት ነው ጥሩ እንቅልፍ አለው አይደል እሱ በጣም ይመቸኛል ነሐሴ ይመስለኛል ዝም ብሎ ውሃ የሚፈሰው ያለ ማቋረጥ ስለዚህ እሱ ይመስለኛል እና እስተኛ ደስ ይለኛል

በተጨማሪ ደሞ ቤታችን ቡና ሲቆላ ዝናብ እየዘነበ ፈንድሻ ሲኖር ቤቱ በጭስ ሲታፈን እሱ ስሜት በጣም ደስ ይለኛል ማዘር ከእቅልፌ ትቀሰቅሰኝና ቡና ፈልቶል ትለኛለች ከዛን እነሳለው ከአልጋ ሳልወርድ ቆሎ እየበላው ቡና እየጠጣው እንጆይ አደርጋለሁ ከእናቴ ጋር እያወራው ማለት ነው ታሪክ ትነግረኛለች እሰማታለሁ ደስ ይለኛል ዝም ብሎ ዝናብ ሲዘንብ ያስጠላኛል ደመና ሲሆን በጣም ነው ሚከብደኝ ፀሐይ ካልወጣች ማለት ነው ዝናብ ዘንቦ ፀሀይ ስትወጣ ደስ የሚል ስሜት አለው፡፡

ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡

ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሽው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?

ተጠያቂ፡- ስሜ ሶስና ይባላል እና ሚሞሬብል የሆነ ወር ለእኔ መስከረም መጀመሪያ ከምወዳቸው በዓላቶች ወይም የሆነ ፊሊንግ የሚሰጠኝ ከእነሱ ውስጥ አንዱ እንቁጣጣሽ ነው እና አንደኛ በእሱ ነው ሚሞቴብል የሆነበት ምክንያት ሁለተኛ የአመቱ መጀመሪያ ስለሆነ የሆነ ኢነርጂ ይሰጣኛል እንዳለ ግሪን ይሆናል አካባቢው ምናምን አዳዲስ

ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡

**ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሸው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?**

ተጠያቂ፡- ስሜ ሄሎን ሰለሞን እባላለሁ ለእኔ የምመርጣቸው ወሮች ከ12 መስረከም አካባቢ ቫይቮን ታውወቃለህ ስለዚህ እኔም እወዳለሁ ከዛን መጨረሻ ወር አካባቢ ደሞ እሱም እንደ መስከም አይነት ነገር ነው ልክ ጳጉሜ አካባቢ ያው ስለዚህ ደስ ይላል ከዛ ውጪ ደሞ በዓላት ያሉበት ፋሲካ ገና ምናምን እነሱ ደስ ይላሉ ከሱ በተረፈ ደሞ በሀሳብ ደረጃ ደሞ ከግማሽ ወር በፊት ያለው ወራቶች ደስ ይላሉ ምክንያቱም ብዙ ነገር ኮምፕልሽ ያደርጋለው በወር ውስጥ ብለህ ታስባለህ ስለዚህ ናቸው

**ጠያቂ፡- ምን ወራቶች ናቸው**

ተጠያቂ፡- አይ ስማቸው በእርግጠኝነት ስለማይመጣልኝ ነው ግን ስድስት አምስት  የሆነ ከ1-6 ወር ደስ ይላል አይም የሎቶል ኮምፕሊሽ ትላለህ 12 ወር ደስ ይላል ወይ 13 ጳጉሜ

**ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡**

**ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሸው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?**

ተጠያቂ፡- ስሜ እራፍ ኃይሌ ይባላል ለእኔ ከ13 ወሩ ለየት የሚለው ነሐሴ የተወለድኩበት ወር ነው ሌላ ደስ የሚሰኝ ነገር ክረምት ነው ብድር ነው ዝናብ ነው እኔ ፐርሰናሊ ይመቸኛል የእሱ ሰሞን ደስ ይላል ብቻ

**ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡**

**ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሸው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?**

ተጠያቂ፡- እኔ ሚካኤል ሽመልስ እባላለሁ ከወራቶች ምመርጠው ወር ሐምሌን ነው ሐምሌና ነሐሴ ነው ምክንያቱም ከራሳችን የምንሰጠው ጊዜ በዛን ሰዓት ሰፊ ነው ሌላ ትምህርት ቢዝ አያደርገንም እና ደሞ አዲስ አመት ለመጀመር የተቃረቡ ጊዜ ስለሆኑ ከራሳቸውን የምንሰጠው ጊዜ ብዙ ስለሆነ ሐምሌ እና ነሐሴን እወዳለሁ፡፡

**ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡**

**ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሸው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?**

ተጠያቂ፡- ስሜ ሚካኤል መለሰ እባላለሁ ለእኔ የምወዳቸው ወራቶች ጥር ሐምሌ እና ጳጉሜ ናቸው ጥር ላይ የአመት በዓል ድባቡ በጣም ከፍተኛ ይሆናል እኔም እምወደው በዓል ጥምቀት ስለሆነ ጥምቀት ወጥተን ማክበሩ እንደ ፋስቲቫል አይነት ነገር ታቦት መሸኘቱ መጠመቁ እነሱ ነገሮች ደስ እንዲል ያደርገኛል ሐምሌ ላይ ደሞ ትምህርት የምናቆምበት እና በዛ ላይ እኔ ሙቀት ስለማልወድ በጋ ቀዝቀዛ ወራት የሚጀመርበት ዝናብ አየሩ የሚስተካከልበት ወቅት ስለሆነ ሐምሌን እወደዋለሁ ጳጉሜ ደሞ ፌሽ ስታርት ይሰጠናል ለአዲስ አመት ዝግጅት አደይ አበቦች ያድጋሉ እና በቃ ኤፍሪቲንግ የአዲስነት የተስፋ የልምላሜ ነገር ስለሚሰጠን ጳጉሜ ደስ ይለኛል፡፡

ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡

ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሽው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?

ተጠያቂ፡- ስሜ አብርሃም ማሞ ይባላል ለእኔ 13 ወራቶች እኩል ነው ይሄኛው ወር ከዚህኛው ወር ይበልጣል ብዬ ማሰበው ምንም ነገር የለም ምክንያቱም ወራቶ ለእኔ የተሰጠኝ ትልቅ ስጦታዎች ናቸው ስለዚህ እኛው ከዚህ አንደኛ ወር ከሌላኛ ወር ይበልጣል ብዬ የማስበበት ምክንያት የለኝም ስለዚህ ስለአንዳንዱ ወር ጭራሽ ምስጋና ነው ያለኝ አመሰግናለሁ፡፡

ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡

**ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሽው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?**

ተጠያቂ፡- ስሜ እሊና ከማል ለእኔ ሚያዚያ ወሩ ሚያዚያ ያልኩበት የተወለድኩበት በተጨማሪ ፋሲካ አንድ ላይ ያለበት ስለሆነ ቤት ውስጥ ካሉ ትልቅ ማማ ከምታደርጋቸው ነገር ውስጥ ፋሲካን በጣም ነው የምታከብረው እና አይ ላይክ ፋሲካን

**ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡**

**ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሽው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?**

**ተጠያቂ፡** ስሜ ብሩክ ካሳዬ እባላለሁ ያው እኔ ጥቅምት ወር ነው በጣም የምወደው ጥቅምት 19 በጣም ምንጊዜም የማረሳው ታሪክ ነው ልጅ የወለድኩት ጊዜ ስለሆነ ደስ ይለኛል በዛ አስታውሰዋለሁ ጥቅምትን

**ጠያቂ፡- ያን ጊዜ ስታስብ ስሜት ይሰጠሃል?**

**ተጠያቂ፡** በጣም ደስ ይለኛል ጥቅምት 19 ሳስበው ደስ ይለኛል፡፡

**ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡**

ጠያቂ፦-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሽው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?

ተጠያቂ፦- ስሜ ዳንኤል ተስፋዬ ይባላል ለእኔ ወራቶች ያን ያህል ሴንስ አይሰጡኝም ይነጋል ይመሻል አንድ ቀን ይመሻል ይነጋል ለእኔ የተለየ ነገር የለም ሰዎች ዝም ብለው የፈጠሩት ነገር ወራት ያን ያህል ስለ ወራት የተለየ ስሜት አይሰጠኝም ጀስት ሰዎች እንትል እንዳለት ነው እንጂ የመምሸት እና የመንጋት ነገር ብቻ ነው ሁልጊዜ የሚታየኝ የወራት ነገር ብዙ ሴንስ አይሰጡኝም

ጠያቂ፦- በመንጋት እና በመምሸት ውስጥ ደሞ የሆነ ባህሪ አለ አይደል ስለ እሱ ባህሪ ምን ታስባለህ?

ተጠያቂ፦- ሁልጊዜ እድል ነው የሚመስለኝ ፐርሰናሊ ማለት ነው እኔ አሁን ለምሳሌ በጊዜያት ሰዎች ይህንን ሲከፋፈሉት ወራት አመታት ሲቀያየር የክረምት የፀደይ ወር ምንናምን ተብሎ ያን ለዛ ለመከፋፈል ታስቦ እንጂ ሰዎች አለ አይደል ወራት ምናምን የሰጡት የመንጋት የመምሸት ነው ሁሉም በዛ ውስጥ የሚፈጠሩ ነገሮች ናቸው ብዬ የማስበው

ጠያቂ፦- አመሰግናለሁ፡፡

ጠያቂ፦-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሽው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?

**ተጠያቂ፡-** እሺ. ፀጋ ዘአብ ነኝ እና ሁሉም ወራቶች በጣም ደስ ይላሉ በይበልጥ ደሞ ሐምሌ ከዛ ደሞ ጳጉሜ ከዛን ደሞ መስረከም ጥቅምት እጅግ በጣም ነው ደስ የሚለው ምክንያቱም ክረምት ጋር ሐምሌ አካባቢ ዝናብ አለ እንደ ሐምሌ ሰማይ ይባላል ሰማይ ይጠቁራል በሐምሌ ጊዜ አንዳንድ ጊዜ ጨረቃ የምትወጣበት ጊዜ አለው ወደ መጨረሻ ማብቂያ ጊዜ ላይ እንደ ታሬስት የሚሆንበት ወቅት አለ እና ያ ደስ ይላል ፍጥረት የሚታከምበት ሰማዩ ይጠቁራል ዝናብ ይዘንባል መሬት ይረሰርሳል የደረቁ ዛፎች በአጠቃላይ ፍጥረት የሚባለው የሚታከምበት ጊዜ ነው ያን ሚሞሪ እወደዋለሁ የክረምት ጊዜ መስረከም ደሞ ከመታከም በኃላ ያለው አዲስ መንፈስ አለው አይደል በአመመ ጊዜ እንደዳንክ የአመመ ሰዓት ጥሩ ጥሩ ምግብ ከዛ በኃላ ባገኘው ብለህ ለራስ ታስባለህ ምክንያቱም ስትድን ሂል እንደምታደርገው ያለው ስሜት በጣም ደስ የሚል ነው እና ምግብ ደንብ ትበላለህ ታጣጥማለህ ልክ እንደዛ ተፈጥሮ ያለህው ነገር ደስ ይላል ከሩቅ ሀገር ወደ ሩቅ ሀገር ስትጓዝ እራሱ ተራሮች ላይ የምታያቸው መልካም ምድሮች ደስ ይላሉ የመስከረም ወር በጣም ቆንጆ ነው በዓላቶች አሉት ደሞ ደስ የሚለው ከእንቁጣጣሽ ጀምሮ መስቀል አስተርዮ ማርያም እንኳን ያሁን መሰለኝ ጥቅምት ደሞ ከመስረከም ቀጥሎ መሰለኝ እሱ ደሞ ደስ የሚለኝ ለምንድ ነው አበቦች የሚያፈሩበት ነው የአበባ ወቅት ነው በጣም ደስ ይላል የጥቅምት አበባ ይባላል ሙዚቃ ላይ ጠዋት አካባቢ ላይ ያሉ መንፈሶች በእነዚህ ወራቶች ላይ አሉ 12-1 ወይም 11-1 ይረጥባሉ ቅጠሎች ይለመልማሉ ጠዋት ካየአቸው ሁሉም ተፈጥሮዎች በተለይ አበቦች ምንም ወፎችን ያላቸው ስሜት ደስ ይላል ቅዝቅዝ ያለ እና የሚያምር ውበት ያለው በእነዚህ ሦስት ወራት ያሉ ለውጦች እንደዚ አይነት ስሜት ስለሚሰጠኝ እወዳቸዋለሁ፡፡

ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡

ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሽው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?

ተጠያቂ፡- ነሐሴ እና መስረከም ማለት የወቅት መቀየር ስለሚኖር ብዙ ሰዎች እና እኔ እናስታውቀሰዋለን ለምሳሌ ተፈጥሮ በእራሶ ውህደት የምታደርገበት ስለሆነ ነሐሴ እና መስረከምን አብልጮ ሚሞሪ ይኖረኛል እናም እወዳቸዋለሁ፡፡

ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡

ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሽው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?

ተጠያቂ፡- ስሜ መልካም ዘሩ ይባላል የምወደው ወር መስረከም ያውም የሚሆንበት ምክንያት ከድሮ ጀምሮ የማስበው ድሪም ነበረኝ እና ለዛ ድሪም ሰክሰስ የሆንኩበት ወር ነው ብዬ አስባለው በአለፈገለግ ሰላም ት/ቤት ተወዳድሬ ያለፍኩበት ጊዜ ስለሆነ ከወራቶች በአጠቃላይ አስበልጬ የምወዳት ወር መስረከም ናት ሌላ ወር የተወለድኩበት ወር ስለሆነ መስረከም መስረከም ብቻ ሞር አስበልጪ የምወደው

ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡

ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሽው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?

ተጠያቂ፡- እሺ አሌክሳደር እባላለሁ ለእኔ ክረምት በተለይ ሐምሌ እና ነሐሴ ምክንያቱም በልጅነት ወራት የመጣልኝ ሚሞሪ እረፍትን ነፃነትን ጨዋታን ደስታን ምንናምን እፈልግ ስለነበር ለእኔ የተለየ ስሜት አላቸው በዛ መሀል ደሞ ቡሄ የፍልሰታ ጾም ያለባት ነሐሴ ወር ለእኔ ልዩ ወር ናት ሞር የበለጠ ለእኔ የተለየ ወር የምለው ነሐሴ የክረምት ወራት ሁለቱን ሐምሌ እና ነሐሴን በተለይ ደሞ ነሐሴን

ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡

ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሽው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?

ተጠያቂ፡- ስሜ አናን ሳሙኤል ይባላል ለእኔ ሚሞሬብል የምላቸው ሁለት ወራት ናቸው በተከታታይ ህዳር እና ታህሳስ ህዳር ያው አንደኛ ልደቴ በዛ ቀን ውስጥ ነው ያው የብዙ ጓደኞቹ ቫሊ የምሰጣቸው

ሰዎች በዛ ውስጥ ስላለ ህዳር በጣም ደስ የሚለኝ ወር ነው ታህሳስ ላይ ደሞ የገና በዓል ስላለ የገና በዓል ያው ክርስቶስ ለእኔ የተሰጠበት ስለሆነ ከምንም በላይ ቫሊዩ የማደርገው በዛው የተወለደች ምርጥ ጓደኛ ስላለችኝ ቫሊዩ አደርገዋለሁ፡፡

**ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡**

**ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሸው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?**

ተጠያቂ፡- ስሜ ዳግማዊ ሙሉወርቅ ነው ከ13 ወሮች ሰኔ እና ጳጉሜ ሰኔ ያው የተወለድኩበት ወር ነው ክረምት ምናምን ስለሚሆን ከክላስ እረፍት ስለሚኖር ፋኬሽን ስላለ እሱ ደስ ይለኛል ጳጉሜ ያው ትንሽ ቀን ስለሆነች አቃታለሁ፡፡

**ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡**

**ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሸው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?**

ተጠያቂ፡- ስሜ ቃልኪዳን ታደለ ከ13 ወር ቫሊዩ የምሰጠው ወር ህዳር ምክንያቱም እኔ እና ወንድሜ እና አብዛኞቹ ጓደኞቼ የተወዱበት ወር ስለሆነ

**ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡**

**ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሽው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?**

ተጠያቂ፡- እሺ እጹብ ድንቅ እባላለሁ ከ13 ወር ውስጥ ሁለቱ ወር ነው የሚያስደስተኛ አሁን ሳስበው እና ህዳር እና ሰኔ ህዳር ላይ የተወድኩበት ስለሆነ የልደቴ ቀን ስለምወደው ህዳር እወደዋለሁ እና በጣም ደስ የሚለኝ ወር ነው ፕላስ ደሞ ሰኔ ደሞ ፍቅረኛዬ የተወደበት እና ከእሱ ጋር አንድ ላይ የሆንበት ስለሆነ እወደዋለሁ እሱንም

**ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡**

**ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሽው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?**

ተጠያቂ፡- ስሜ ሩት ነው እና ከሁሉም ወራት የምወደው ግንቦትን ነው አንደኛ ምክንያቴ ክላስ አልቆ ማርፍበት ሰለሞን ነው በክላስ ደክሜ ሳርፍ ደስ ይለኛል ሁለተኛ ምክንያቴ ደግሞ ግንቦት ልደቴ ነው እና በቃ እረፍት ፕላስ ልደት የማከብርበት ሰሞን ስለሆነ እንደገና የብዙዎቹ ቤተሰቦቹ የጓደኞቹ የልደት ሰሞን ያን ጊዜ ስለዚህ ግንቦትን እወደዋለሁ፡፡ ከግንቦት በኃላ እስከ መስከረም ያለው እወደዋለሁ፡፡

**ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡**

ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሽው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?

ተጠያቂ፡- ስሜ ኪሩቤል ስንታየሁ ይባላል ከ13 ወራት ውስጥ ሰኔ ወርን ደስ የሚለኝ ይመስለኛል አንደኛ እኔም የተወለድኩበት ወር ነው ሁለተኛ ከፍቅረኛዬ ለመጀመሪያ ጊዜ ፍቅር የጀመርንበት ወር ነው እናም ኖርማሊ ሰኔ ደስ ይለኛ ብቴክ ብዙ ጊዜ ስላለ

ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡

ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሽው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?

ተጠያቂ፡- ስሜ ሶስና ይባላል እና ለእኔ ሚሞሬብል የሆኑት ወራቶች ውስጥ የመጀመሪያው መስከረም ነው መስረከም ያልኩበት ምክንያት አንደኛ የወሩ መጀመሪያ ነው እና የሆነ ኢነርጄቲክ ያደርገኛል ለእኔ ሁለተኛ ደግሞ መስረከም ላይ ያው እንቁጣጣሽ በዓል አለ እና ለእኔ ስሜት ከሚሰጡኝ በዓላቶች ውስጥ አንዱ እንቁጣጣሽ ነው የሆነ አይነት ስሜት የፍጥራል እኔ ጋር የሆነ ጭንቅ ነገር ምናምን የማለት ስሜት ይሰጠኛል ለእኔ የሆነ ብቻ ሚሞሬብል ነው በእሱ ምክንያት መስረከምን ለእኔ ሚሞሬብል ነው ወር ነው እልላሁ እና ደሞ ሌላ ምንድን ነው መስረከም የወሩ መጀመሪያ እንደመሆኑ ብዙ ሰዎች የሆነ አዳዲስ ስራ የሚጀመሩበት አካባቢው የሚቀየርበት የተለያየ አበባ ይበቅላል ግሪን ይሆናል ሂርያው ምናምን ሶ አንደኛ እሱ ደሞ ጽዱ ይመስላል ወሩ እራሱ መስረከም የሚባለው ወር ሲታሰብ ለእኔ ንጹሁ ወር ይመለስለኛል

እና እሱ ይመቸኛል፡፡ ለእኔ ሚሞሬብል ነው እና ደሞ ሌላ ሚመቸኝ ወር ሰኔ ነው ምክንያቱም የተወለድኩበት ዓ.ም ስለሆነ አሚን ወር ስለሆነ እና ደሞ ክላስ የምንጨርስበት ወደ እረፍት ምንሄድበት ስለሆነ ሰኔ ይመቸኛል ክረምት አልወድም፡፡

**ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡**

**ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሽው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?**

ተጠያቂ፡- እሺ መስረከም ጣሰው እባላለሁ ልክ እንደ ስሜ መጀመሪያ የምወደው ወር መስረከም ነው አየሩ ደስ ይለኛል በጣም አበባዎች ምናምን አሪፍ ስሜት ይሰጡኛል ግን ደግሞ ያመኛል በአበቦቹ ሽታ ምክንያት ሳይነስ አለብኝ ያመኛል ግን እንደዛውም ሆኖ እሱ ነው የምወደው የምጠላው ወር ደግሞ አለ ግንቦት በጣም ስለሚሞቀኝ እና የአካባቢው አረንዴነት ስለሚጠፋ ይደብረኛል፡፡

**ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡**

**ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሽው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?**

ተጠያቂ፡- እሺ አመሰግናለሁ ስሜ ተስፋ ማርያም ይባላል እኔ የምወዳቸው ወሮች ሁሉንም እወዳለሁ ነገር ግን ሁለቱ ወር ልምረጥ የካቲት

ወር እና መስረከም መስረከምን ያልኩበት ምክንያት የዘመን መለወጫ ነው በእኛም ሀገር እና የጸደይ ወርም ነው ብዙ ነገሮችን አበቦች የሚፈነዱበት በደንብ ከለር ፉል እይታ የምናይበት ጊዜ ነው አንደኛ መስረከም ሁለተኛ ደሞ የካቲት ወር የነፃነት ቀን ነው ለእኔ አድዋ ድል ያለበት ወር ነው ሁለቱን መርጫለሁ አመሰግናለን፡፡

**ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡**

**ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሸው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?**

ተጠያቂ፡- ስሜ ሻሎም ወንድሰን ይባላል ለእኔ ለየት ያለ ወር የምነው ታህሳስ ነው እሱም ምክንያቱም ቤተሰቦቼ ታህሳስ እንደወደው ያደረገው ልደቴም የእኔም የእህቴም የከበርልን ነበር እና በጣም ………………ያኔ የነበረን ሳይድስ ደሞ ገናም አለ እናም እነዚህን ነገሮች ይህንን ወር እንድወደው አድርጎኛል ዚ ሲስ በሲክሊ የምወደው ከ13 የምወደው ታህሳስን

**ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡**

ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሸው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሸበት/ክበት ወር የትኛው ነው?

ተጠያቂ፡- ሰላም አዲስ አለማየሁ እባላለው ስለወራቶች ያሉኝ ሲሎንጎች አንደኛ ከወራቶች ያሉኝ ሚሞሩል ጥር ነው አሁን ያለንበት ወር ነው አብዞም ጥር ከ11 በኃላ የጥምቀት ባህልን ያለው ለእኔ በጣም በጣም ብዙ ሚሞሪ ያለበት ነው ለምሳሌ ሴሪብሽን አለ ጥምቀት በአል አለና ብዙ ….እንዳስታውስ አመታት እንደውም አንድ አመት አልፎ ሌላ አመት ሲመጣ ሁሌም የሚናፍቀኝ ወር ቢኖር ጥር ነው ያንን ጥምቀት በኣል በደንብ ከጥር ጋር የለኝ ጥምረት በጣም ለየት ይላል ተፈጥሮዬም ይመስለኛል ጋር ጸሀይማ ካለኝ ከጤናም ጉዳይ አንጻር አስም በሽተኛ ስለሆንኩኝ ለጤንነቴ የሆነ ጊዜ የጸሀያማ ጊዜ ቆንጆ የሚሆነ የጥር ወር እና ሌሎች ወራቶች ሲመጡ ይከብዱኛል ለምሳሌ ሐምሌ አይመችም እስከ ጥር ወር ያለው ለእኔ በጣም ከባድ የሆነ ሙመት ነው የአየር እንቅስቃሴዎቹ ከጤና ጋር ጥር ሲመጣ ፀሀይ የሚወጣበት ጊዜ ነው አረንጓዴ የሆነ የሚታይበት ሙመት ነው ናቸው ሁሉም ነገር ጥር ጋር ያለኝ አታችመንት ከጤንነትም አብሶ ከጥምቀት ጋር ያለኝ ሚሞሪ በጣም ለየት ያደርገዋል፡፡

ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡

ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሸው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሸበት/ክበት ወር የትኛው ነው?

ተጠያቂ፡- ስሜ ሳምሶን ተስፋዬ ይባላል ታህሳስ የቤተሰብ ኢሹ ነበር የሀገራችን በተፈጠረው ነገር ግጭቶች ነበር አን ጎርፈርት ይሰማኝ ነበር ያስጨንቀኝ ጊዜ ነበር እዛ ጉዳይ ውስጥ ሽሽት ነገር ውስጥ

ነበርኩ ታህሳስ አስጨናቂ ጊዜ ነበር ለትምህርቱ እየራኩ ነበር ለዛ ነው፡፡

**ጠያቂ፡- እንዴት ትገልጻታለህ አስጨናቂዋን ጊዜ**

ተጠያቂ፡- ያው አሁን ለቃለ መጠየቁ ነው እንጂ ማስታወስ አልፈልግም ወሩ ያስጠላኛል፡፡

**ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡**

**ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሽው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?**

ተጠያቂ፡- ስሜ አቤል ተስፋዬ አሁን ያለነው በአጋጣሚ ጥር ወር ላይ እና ከጥር ወር ጋር ተያይዞ ከእኔ ጋር ያለው ሚሞሪ ምንድነው የጥምቀት በአልን አስመልክቶ ምን ይባላል ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚ ይበጣጠስ ይባላል እና ሰዎች ከከተራ ጀምሮ እስከ ቀጣዩ በዓል ድረስ የሚያደርጉት ዝግጅት በአለባበስ ሊሆን ይችላል በሌሎችም ነገሮች ሄደው በኣልን አክብረው እንጆይ አድርገው ተደስተው ትዳር ፈላጊው ሁሉ ጥር ወር ላይ ሎሚ ሁሉ የሚያዘጋጁበት ወቅት ላይ ነው የሚወረወርበት ትውውቅ የሚደረግበት ነው እርስ በእርስ ወጣቶች የሚተጫጩበት ነው አንዱ አጋጣሚ በዛ ደሞ ጥር ወር ትልቅ ወር ነው ከሃይማኖትም አንፃር ስታየው ክርስቶስ በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠምቆ የሰው ልጅን የእዳ ደብዳቤ የቀደደበት ወይም የሰረዘበት ወር ስለሆነና በዚህ ወርም በዓሉ ስለሚታሰብ ከዚህ ጋር

ተያይዞ ይሄ ሚሞሪ አለኝ በዓላዊ እሴቶች አሉ አሁን ጥምቀት የሚከበረባቸው ከተራ ታቦት የሚያርፍባቸው አካባቢ ስትሄድ ለበዓል ነው በእርግጥ በሃይማኖቱ ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም በዓል ብዙ አይነት ጌሞችን ታያለህ ብዙ አይነት ኢንጆይመቶችን ታያለህ ያ ነገር አይምሮ ውስጥ ስላለ ከጥር ወር ጋር ያ ነገር ይገናኝልኛል፡፡

**ጠያቂ፡- ስለ የካቲት የምታስበው አለው አንድ ነገር ብትጨምርልኝ?**

ተጠያቂ፡- አዎ የካቲት ሲባል እኔ ታሪክ ነው ከታሪክ የካቲት 12 ማርሻል ፕራዙላዊ ንጽሁዋን ኢትዮጵያዊያንን የጨፈጨፈበት እና ያስጨፈጨፈበት ወቅት ነው እና የካቲት 12 ሲባል ትዝ የሚለኝ ሀውሉቱ 6 ኪሎ ያለው ሀውልት ትዝ ይለኛል ገዛኛልም ፊል አድርገዋለሁ ያ መሰዋትነት ያለ አግባብ የተደረገ ግፍ ያ አግባብ የፈሰሰ ደም ትዝ ይለኛል እና በዛ አስበዋለሁ

**ጠያቂ፡- አቤል በጣም አመሰግናለሁ፡፡**

**ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሸው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?**

ተጠያቂ፡- እሺ ስሜ ዳዊት ሰለሞን ይባላል በጠየቀኝ ጥያቄ መሰረት ጥርን ሳስታውስ በብዛት የሚመጣልኝ ያለፉት ሦስት አመትት በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ ጥምቀትን ታቦት በማጀበት በፊት ለፊት በመሆኑን ማህበር ውስጥ አጅብ ነበር እና ጥር ሲመጣ የሚታየኝ አራቱን ቀናቶች ስንዘምር ፀሀዩንም ዝማሬው የጥምቀት ማጀቡን ይሄ ነገር ትዝ ይለኛል

ጠያቂ፡- ስለ የካቲት ሚሞሪ አለህ የካቲትን ስታስብ አለህ?

ተጠያቂ፡- የካቲትን ሳስብ ሰርግ አምናም ሚዜ ነበርኩ አምና እና የካቲት በብዛት የሰርግ ታይም ስለሆኑ እና የሰርግ ጊዜያቶች ደስ ይሉኛል ከጓደኞቼ ጋር ብቻ እሱነቱ ደስ ይለኛል፡፡

ጠያቂ፡- እሺ አመሰግናለሁ ዴቪ፡፡

ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሽው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?

ተጠያቂ፡- አመግናለሁ ስሜ ጴጥሮስ ሰለሞን ይባላል ጥር ላይ ነው አይደል ያልከኝ ጥር ላይ ያለኝ ትውስታ የስራ መጨናነቅ ነው የበዓላት ሰሞን ስለሆነ ሰዎች ለሰርጎቻቸው ልብሶችን የሚያዙበት እንዲሁም ለጥምቀት ልብሶች የሚታዘዙበት የገና በኣላትም ላይ ልብስ የሚታዘዝበት ኦርደር የሚበዛበት ነው በአጭሩ ስራ የሚበዛበት ስለሆነ በጣም የምጨናነቅበት ሰዓት ነው በትምህርቱም ደሞ ትምህርት እና ስራ ስለሆነ ሁሌ በየአመቱ የምታመምበት ታይሚንግ ላይ ነች ይች በጣም እስትረስ የሚበዛበት ሰአት ነው ይህን ይመስላል፡፡

ጠያቂ፡- የካቲት ወር ላይ ሌላ ሚሞሪ አለህ?

ተጠያቂ፡- የካቲት ወር ላይ ደሞ የካቲት 13 ልደቴ ነው ሀፒ ፐርስደይ ትላለህ እንዳትረሳው አንድ እሱ ሁለተኛ ደሞ በጣም በኢትዮጵያ ውስጥ ትልቅ ነገር የተከናወነበት ወይም ደሞ ትልቅ መሰረት

ለሆንበት ለእኛ ለአደዋ በዓል እና ለጥቁር ህዝብ ኩራት ስለሆነ ይንን ቀን አስታውሰዋለሁ ትልቁ ትርጉም አለው፡፡

ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡

ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሽው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?

ተጠያቂ፡- ስሜ መጀመሪያ ልዑል ሰይፉ አማረ ገ/ሕይወት አውግቼው እስከ ማውቀው ድረስ እና እኔ የሚመቸኝ ወር 13 ወሮች እንጃ ጳጉሜ እንደ ወር ከቆጠርካት ኤኒ ወይስ የሚመቸኝ ወር ሚያዚያ ነው ለምን ብትል ሚያዚያ እንጃ ትልቁ ወር ነው ትልቁም በዓል ፋሲካ በዓል ወድጄ ሳይሆን ላይክ ለበዓሉ ትርምስ ሰው የሚያደርገው ነገር በጣም ኢንተርስቲንግ ያደርገኛል እኔ ስለማላደርገው እሱ ብቻ አይደለም ሌላም በዓሎች አሉት ትናንሽ በዓሎች እነሱም አሉ እነሱም ተደምሮ የእኔም ልደትም አለ ሚያዚያ ውስጥ ነው የተወለድኩበት እና በጣም ሰልፍሽ እንዳይመስል ግን ልደቴን በጣም ነው የምወደው እዚህ አለም ላይ ሪክፔክት የማደገው እኔንና እኔን ብቻ ነው ግን ሰልፍሽ ነው የምመስለው ግን ለእኔ ልደቴ ባይዘዌ ፐርሰናል ካላንደር ነው የምጠቀመው አመቱ የሚጀምረው እኔ የተወድኩበት ወር ላይ ነው ስለዚህ አዲስ ዓመት ለእኔ ሚያዚያ ውስጥ ከሚያዚያ ጀምሮ የምቆጥረው ምክንያቱም ስፔሻሊ የእኔ ካላንደር ያኔ ነው ያእኔ ነው የተወለድኩት ስለዚህ ኔክስት ይር ብዬ

የምቀጥለው ከዛን ድጋሜ ሚያዚያ ሲደርስ ነው ሶ ሳት ዋይ ለእኔ ሚያዚያ ስፔሻል ነው የሆነው፡፡

ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡

ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሽው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?

ተጠያቂ፡- ስሜ ቢታንያ ታዬ ይባላል ለእኔ ሚሞሬብ የሆነው ቀደም ብዬ የማስበው ወሮች ውስጥ ጥር ወር ነው ምክንያቱም አንደኛ ነገር ድሮ ከአይስኩል ጀምሮ ከአይስኩልም በፊት ልክ የሴሚስቴር ፕሬክ የሚሆንበት በተጨማሪም የልደቴ ወር ስለሆነ የምመርጠው ወር ጥር ወር ነው፡፡

ጠያቂ፡- ሌላ በበዓል ሚሞሪ አለህ?

ተጠያቂ፡- አዎ በበዓል ታህሳስን እመርጣለሁ የሚገርመው ተከታታይ መሆናቸው ግን ታህሳስ ላይ ያለው አየር ይቀየርብኛል ከገና ጋር ስለተያያዘ ብቻ ሳይሆን ጥሩ አውቶፍስፌር የሚመስል ደስ የሚል ቫይቮ ያለው ለእኔ ታህሳስ

ጠያቂ፡- ሌላ ይኖራል የካቲትን ብትጨምርልኝ ወይም ሌላ የራስክ ሚሞሪ ያለህን ብትጨምርልኝ?

ተጠያቂ፡- ሌላ ወደ መስከረም ወር ላይ እሱም ጀስት አብዛኛውን በጥሩ ላይሆን ይችላል በፊት ላይ ልጅ እያለሁ ይመረኛል ልክ

መስከረም ሲደርስ አሁን ግን መስከረም ላይ አዲስ ነገር ጥሩ መስሎ ስለሚሰማኝ ጥሩም ያው እንተለመደው ከበዓል ጋር ስለምናከብርበት መስቀል በጣም እወዳለሁ፡፡

**ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡**

**ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሽው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?**

ተጠያቂ፡- እሺ ስሜ ናሆም ሱራፌል ይባላል ከ13 ቱ 13ተኛ ጳጉሜ ይጨንቀኝ ነበር ምክንያቴም ክረምቱ ሊያልቅ ትምህርት ቤት ልንገባ ነው የመጫወቻ እንትትኑ ሊያበቃ ነው እና ጠዋት ጠዋት ጳጉሜን ጸበል ታስጠምቀን ነበር  እናቴን በቃ ጳጉሜ ሊመጣ ሲል የሆነ የማይሆን ስሜት አለኝ

**ጠያቂ፡- ለአንተ ደሞ ሌላ ስሜት የሚሰጥ ጊዜ?**

ተጠያቂ፡- ህዳር ልደቴ ስለሆነ ከጥቅምት ጀምሮ እየቆጠርኩ እጠብቀሃለሁ

**ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡**

**ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሸው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?**

ተጠያቂ፡- እሺ ስሜ አቤል ተስፋዬ ይባላል ከ13 ወራቶች መስረከም ልዩ ወር ናት ለእኔ ልክ ክረምቱ አልቆ ጳጉሜ መጨረሻዎቹ ሲደርስ መስረከም በጉጉት ነው ምጠብቃት ለእኔ ምንም ባይፈጠር ምንም ባይደረግ አዲስ ኢነርጂ ይሰጠኛል አዲስ ለውጥ እራሴ ላይ አድርግበታለሁ እና እሱን ስሜት በጣም ነው የምወደው በጣም ነው ምጠብቀው ከአመት አመት መስረከም አንድ በተለይ በጣም ልዩ ስሜት አላት ለእኔ ባላከብረውም ባከብረውም ቀኑ ልክ ሲደርስ ልዩ ስሜት ይሰጠኛል ኢነርጂ እና መስረከም አንድ ልዩ ቀን ናት፡፡

**ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡**

**ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሸው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?**

ተጠያቂ፡- ስሜ አማኑኤል አዲስ ይባላል ምወደው ወር ህዳር የተወለድኩበት ወር ስለሆነ እና ልደታም ወር ስለሆነች ደስ ይለኛል የምወደው ወር እሱ ነው፡፡

**ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡**

ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሽው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?

ተጠያቂ፡- ኦኬ ሂለን ደረጀ ይባላል ከ13 ወራት ለእኔ የተለየ የምለው ህዳር ወር ነው 3ተኛው ወር አንደኛው የልደቴ ቀን ነው ፕላስ የተለያዩ እምነታዊ ክብረ በዓላት አሉ የአመት ንግሶች እነሱ እነሱን ሳስብ የተለየ ስሜት ይሰጠኛል እና የበኣል አይነት ስሜት ስለሚሰማኝ ፕላስ ወረሃ ጽጌ ስለሆነች ለእኔ ያቺ ተለየች ወር ናት አመሰግናለሁ፡፡

ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡

ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሽው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?

ተጠያቂ፡- እሺ ስሜ ወ/ሮ ......እባላለሁ አሁን ትዝታዎቼ 13 ወራት ግንቦት ሦስትን 81 አንድ ትዝታ አለኝ እሱም ክንፈ ሚካኤል እንደወለድኩኝ በ8 ቀን መንፈንቅለ መንግስት እንደገና ደግሞ በ15 ቀን ደሞ ዋርካ ወድቆብኝ እሱ ትዝታ ነው አምስት ቤተሰብ ሆኜ ወድቆብኝ ገብርኤል እንደሆነ አድኖኛል ገብርኤል አድኖኝ ትዝታ ሁልጊዜ አነሳዋለሁኝ እና በእኔ እድሜ ከቀደቀብኝ በኃላ በእኔ እድሜ ድምስ ምሱ ጠፋ ዋርካው እናም መብራትም ቀድቆብኝ ነበር ዋርካ ጥሎብኝ እግዚአብሔር ያዳነኝ መላከ ቅዱስ ገብርኤል አባቴ አድኖኝ አሁን አወጋዋለሁኝ አወራዋለሁኝ

ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡

ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሽው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?

ተጠያቂ፡- ስሜ ብስራት ይባላል ማለት ጥቅምትን ሳስባት እራሱ በጣም ነው የሚጨንቀኝ ማስታወስ ሁሉ አልፈልግም ለምን አልፈልግም በሕይወቴ ውስጥ በጣም ትልቅ የሆነ የሀዘን አሻራ ነው ጥሎብኝ ያለፈው ወር ነው እናቴ ከእናቴ በላይ ናት ብላት ይቀለኛል ያሳደገችኝ ነገሯን ሁሉ ትታ ለእኔ የሆኖረች ሰው ናት እና በዛወር ነው እሷን ያጣዋት እና ማስታወስም አልፍልግም ጥቅምት 12 ነው የሞተችው ለእኔ ብቻ አይደለም ሙሉ ለቤተሰቤ ዋጋ ከፍላለች በቃ ሰው ሀገር ተንከራታለች እሷ ሳትበላ እኛን አብልታለች እና ይቆጨኛል እኔ የሆነ ቦታ ላይ ደርሼ እሷ የምትፈልገው አይነት ሰው ሆኜ ባለማለፏ ነው፡፡

ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡

ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሽው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?

ተጠያቂ፡- አመሰግናለሁ ክንፈሚካኤል ደረጀ እባላለው ጥቅምት ሲነሳ ከአእምሮ ላይ የማይጠፋው ቅዝቃዜው ነው ወቅቱ በጣም ብርዳማ ነው በተለይ ወደማታ አካባቢ ላይ አዳሩም ከባድ የሆነ ንፋስ እና በጣም በጣም ከባድ የሆነ አጥንት የሚሰብር ቅዝቃዜዎች አሉ እና ጥቅምት ወር ሲመጣ ሁሌ አእምሮ ላይ የማጠፋው ቅዝቃዜ ነው ለእሱ የሚደረገው ዝግጅት አልባሳት አመጋገብ ከተለያዩ ነገሮች

አንጻር ለእሱ የሚደረጉ ነገር ሁሌም አእምሮ ላይ ይመጣል እራሴም ላይ

**ጠያቂ፡- ከዚህ የለየበት ሌላ አይነት ሀሳብ የምታገኝበት ነገር አለ?**

ተጠያቂ፡- ከዚህም የተለየ ብዙም የለውም ኖርማሊ ከመቶ 99 ፐርሰንት የለውም አንድ ፐርሰንት ግን ዘንድሮ ላይ ፈጽሞ ላገኘው የማልችለውን ድል አገኛዋለሁ ብዬ ያላሰብኩትን ድል ጥቅምት ላይ አግንችበታለሁ ከእግዚአብሔር ጋር ጥሩ ነገር የማስበው እሱን ነው በተረፈ ግን ተማሪ በነበርንበት ሰዓት የሆነ ነገር ሊኖር ይችላል አሁን ግን የማስታውሰው ሁሌም አእምሮ ላይ የማይጠፋው የጥቅምት ቅዝቃዜ ነው እና ያው አባባል አለ በጥቅምት አንድ አጥንት ቅዝቃዜን ለማሸነፍ የሚባለው ነገር እሱ ሁሌም አእምሮ ላይ አለ

**ጠያቂ፡-** ደሊ ያልከው ነገር ኢትዝ ዘ ፕራይበቴ ኦር ፐብልሽ የምታደርገው ነገር ሜቢ ፕራይበት ካልሆነ?

**ተጠያቂ፡-** ፕራይቤት ብቻ ሳይሆን የቤተሰብ ታሪክ ስለሆነ ነው ቤተሰቤም ድል ያገኘበት ነው ለረጅም ጊዜ ስታገልበት ስንታገልብት የቆየነው ግን እግዚአብሔር አምላክ ደግሞ በቃ ብሎ በወሩ የመጀመሪያ ቀን ላይ ድልን የነሳንበት ድል የተደረገበት እለት ነው፡፡

**ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡**

**ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሸው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?**

**ተጠያቂ፡-** እሺ አመሰግናለሁ ስሜ መንዝወቅር ደረጀ ይባላል መጋቢት ወርን ሳስብ ማለት ማንኛውም ኢትዮጵያ መጀመሪያ የሚመጣለት ከሃይማኖት ጋር የተያያዘ ታላቁ ጾም አብይ ጾም ወይም ሁዳዴ እሱን በቀጣይነት ደግሞ የጌታች የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አመታዊ ክብረ በኣል መጋቢት 27 መድኃኒዓለም እነዚህ አስታውሳለሁ በግል ደግሞ ይሄ ነው የምለው ሚሞሪ የለኝም ከሃይማኖት ጋር የተያያዘ ነው እነዚህ ጊዜያቶች ያስታውሰኛል አመሰግናለሁ፡፡

**ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡**

**ጠያቂ፡-ስምህ/ሽ እና ከ13 የኢትዮጵያ ወራት ላንቺ የምታስታውሸው/ታውሰው ጥሩ ጊዜ ያሳለፍሽበት/ክበት ወር የትኛው ነው?**

ተጠያቂ፡- ሰላም ስሜ ነብዩ አብደላ ይባላል ከ13 ወራት ውስጥ ለእኔ ልዩ ወይም ደግሞ የማስታወሳት ወር መጋቢትን ነው ይህችም ምክንያት የሆነችኝ የወንድሜ ታላቅ የሆነው ወንድሜ በጣም የምወደው ወንድሜ ለእኔ ብዙ ውለታ የከፈለልኝ ወንድሜ የተወለደበት ወር ስለሆነ ለእኔ ልዩ ወሬ ነው የወንድሜ መታሰቢያ ወር አድርጌ ስለምቆጥረው መጋቢትን ለእኔ ልዩ ጊዜ ነው፡፡

**ጠያቂ፡- አመሰግናለሁ፡፡**